# ደንብ

# ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ፅሁፎች፡- ECJ–RA, JPC–RA, JPD, JPD–RA, JPF–RA
ሀላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡- ልዩ ትምህርት እና የተማሪ አገልግሎቶች
ተዛማጅ ምንጬ፡- አባሪ የሜሪላንድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-426 (ED §7-426) እና ተከታዮቹ ገፆች፤ የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ 13A.05.05.05-.15

## አናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ለአጋጠማቸው ተማሪዎች የአደጋ ጊዜ እንክብካቤ

I. ዓላማ

ለማንኛውም አናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ለታመመ ተማሪ የአደጋ ጊዜ ህክምና እንክብካቤ ለመስጠት ቅደም-ተከተሎችን ማስቀመጥ፣ ይሄም የወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ተማሪዎች፣ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ጤና ክፍል እና በሰው አገልግሎቶች የት/ቤት ጤና አገልግሎቶች (SHS) ትብብር ነው

II. መነሻ-ዳራ

አንዳንድ ተማሪዎች ለነፍሳት መርዝ፣ ለምግቦች፣ ወይም አካባቢው/ምህዳሩ ውስጥ ለሚገኙ ሌላ ንጥረ ነገሮች ከባድ፣ ለህይወት አድጊ የሆነ አካላዊ ምላሾች (reactions) አላቸው እና አናፊላክሲስ (Anaphylaxis) የሚባል በሽታ በፍጥነት ይከሰትባቸዋል። እነዚህ ተማሪዎች ወደ ሆስፒታል መዳኃኘ እየጠበቁ ባለበት ወቅት ወዲያውኑ ኤፒንፍሪን (epinephrine) መወጋት ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

አናፊላክሲስ (Anaphylaxis) መሆኑ/ኗ ለታወቀ ወይም ምልክት ለሚታይበት/ባት ማንኛውም ተማሪ እያንዳንዱ የአካባቢው ት/ቤት ዲስትሪክት የት/ቤት ነርስ እና ሌላ የሰለጠነ ሰራተኛ አውቶማቲክ-መውጊያ ያላቸው ኤፒንፈሪን (epinephrine) መስጠት እንዲፈቅዱ የሜሪላንድ ህግ ያዛል። የት/ቤት ሰራተኞች የአናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ምልክትን እንዴት ማወቅ እንደሚችሉ፣ አውቶማቲክ-መውጊያ ያላቸው ኤፒንፈሪን (epinephrine) የመስጠት ቅደም-ተከተሎችን እንዲዘጋጁ፣ የአደጋ ጊዜ ቅደም-ተከተሎችን በተገቢው መንገድ መከተያ መንገድ እንዲያዘጋጁ፣ እና የት/ቤት ነርስ በአደጋ ጊዜ ሁኔታ ውስጥ መጠቀም እንዲችሉ በፐብሊክ ት/ቤት አውቶማቲክ-መውጊያ ያላቸው ኤፒንፈሪን (epinephrine) እንዲይገኙ እና እንዲያስቀምጡ ዲስትሪክቶች ስልጠና እንዲሰጡ ይጠበቃል።

III. ትርጉም

A. አናፊላክሲስ *(Anaphylaxis)* ማለት አንድ ግለሰብ ለአለርጂ ተጋላጭ ሲሆን/ስትሆን የሚፈጥር ድንገተኛ፣ ከባድ፣ እና ለህይወት አደጋ ሊፈጥር የሚችል የአለርጂክ ምላሾች (reaction) ነው።

B. አውቶማቲክ-መውጊያ ያላቸው ኤፒንፈሪን *(epinephrine)* ማለት በአደጋ ሁኔታ ውስጥ አናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ለማከም የሚጠቅም ቀድሞ የተለካ አንድ ጊዜ የሚወሰድ ኤፒንፈሪን (epinephrine) ያለው ለመያዝ አመቺ፣ ተጠቅሞ የሚወገድ የመድሀኒት መስጫ መሳሪያ ነው።

## IV. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. ስልጠና

የት/ቤት ሰራተኞች አናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ሊያጋጥማቸው ለሚችሉ ተማሪዎች ዝግጁ ለመሆን ሰልጥነዋል፣ ተማሪው/ዋ ከአሁን በፊት አናፊላክቲክ (anaphylactic) አለርጂ ያጋጠማቸው ሆነም አልሆነም ወይም የኤፒንፈሪን (epinephrine) መድሀኒት ትእዛዝ ስልጣን ከተሰጠው ፈቃድ ያለው የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ያላቸው ቢሆንም ነው።

1. የልዩ ትምህርት እና የተማሪ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (OSESS) አጠቃላይ የግንዛቤ ስልጠና ግብዓቶችን እና የመረጃ አያያዝ ቅደም-ተከተሎችን የማዘጋጀት ሀላፊነት አለበት። ሁሉም ት/ቤት-መሰረት ያደረጉ ሰራተኞች፣ የባስ ሹፌሮች፣ እና የባስ እረዳቶች የአናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ምልክቶችን መለየት እንዲችሉ አጠቃላይ የግንዛቤ ስልጠና ይሰጣቸዋል።

2. ዳይሬክተሩ/ሯ፣ ከት/ቤት ማህበረሰብ ጤና ነርስ (SCHN) ጋር በመመካከር፣ የአናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ማሳያዎችን እና ምልክቶችን መለየት እንዲችሉ ስልጠና የሚቀበሉ እና፣ በተጨማሪም፣ አውቶማቲክ-መውጊያ ያላቸው ኤፒንፈሪን (epinephrine) አሰጣጥ ስልጠና የሚወስዱ በጎ ፈቃደኛ የሆኑ ት/ቤት-መሰረት ያደረጉ ሰራተኞች የመለየት ሀላፊነት አለባቸው።

   a. የተመረጡ ሰራተኞች ማካተት ያለባቸው ዳይሬክተሩን/ሯን ወይም ሌላ አስተዳዳሪን፣ እና ቢያንስ ሁለት ተጨማሪ ት/ቤት-መሰረት ያደረጉ ሰራተኞችን ነው።

   b. ዳይሬክተሮች፣ የሚቻል ሲሆን፣ ለመጀመሪያ እርዳታ እና ልብና ሳንባ ቀጥ በሚልበት ጊዜ የማስነሳት/ማንቃት (cardiopulmonary resuscitation) ስልጠና የሚወስዱ ሰራተኞችን መምርጥን ማሰብ አለባቸው።

   c. ኤፒንፈሪን (epinephrine) አሰጣጥ ስልጠና ለመውሰድ የሰራተኛ ስምምነት በበጎ ፈቃድ ላይ የተመረከዘ ነው።

   d. MCPS እና SHS የአናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ምልክቶችን የመለየት ስልጠናን ለመስጠት እና ለመቆጣጠር እና አውቶማቲክ-መውጊያ ያላቸው ኤፒንፈሪን (epinephrine) ለመስጠት በመተባበር ይሰራሉ።

3. ተገቢ የሆኑ የሰራተኛ አባላት የሚታወቅ አናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ለአለባቸው ተማሪዎች የግል ጤና እንክብካቤ ዕቅዶች ላይ ስልጠና ይወስዳሉ። የሚታወቅ አናፊላክሲስ (Anaphylaxis) ለአለባቸው ተማሪዎች የግል ጤና እንክብካቤ ዕቅዶች የበለጠ ተብራርተው የሚገኙት በአንቀፅ

/ Section IV.B።

B. የሚታወቅ አናፊላክቲክ (Anaphylactic) አለርጂዎች ለአለባቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉ ሰነዶች፣ መድሀኒት፣ እና የአሰጣጥ መሳሪያዎች።

1. SCHN፣ ከ MCPS ጋር በመተባበር፣ ለነፍሳት መርዝ፣ ምግቦች፣ ወይም ሌላ ንጠረ ነገሮች የሚታወቅ አናፊላክቲክ (Anaphylactic) ምላሾች (reactions) ለአለባቸው ተማሪዎች በት/ቤት ኮንፈረንሶች፣ በጤና መዛግብት ግምገማ፣ በወላጅ/አሳዳጊ ሪፖርቶች፣ በህክምና ባለሙያ፣ ወይም በግል-ጥቆሞ በመጠቀም ይለያሉ።

2. ልዩ የጤና ፍላጎቶች የአለው/የአላት የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ በሜሪላንድ ህግ / Maryland law ED §7-426(b)(2) መሰረት የሚከተሉት ሀላፊነት አለበት/ባት፦

   a. የተማሪን የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ወይም ምርመራዎች በሚመለከት ለት/ቤት የማሳወቅ

   b. ተገቢ መድሀኒቶችን እና የመስጫ መሳሪያዎችን ማቅረብ

   c. ለመድሀኒት እንዲሰጥ መስማማት

3. የሚታወቅ አናፊላክቲክ (Anaphylactic) ምላሾች (reactions) የአለበት/ባት ተማሪ ሲለይ፣ SCHN እና፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ ዳይሬክተሩ/ሯ ወይም ተወካይ፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር በመሆን ተማሪ በትምህርት ቀን ውስጥ ሊያጋጥመው/ማት የሚችሉ ድንገተኛ የህክምና ሁኔታዎች በአመታዊነት ለመዘጋጀት ይሰራሉ።

   a. አሁን ላይ የአለን ዶክተር ትዕዛዝ ማግኘት፣ MCPS ቅፅ 525-14፦ በምርመራ አናፊላክሲስ *(Anaphylaxis)* የተገኘበት/ባት ተማሪን የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤን ማድረግ፣ ይሄም በጤና ባለሙያ እና በወላጅ/አሳዳጊ የሚፈረም እና በየአመቱ የሚስተካከል ነው

   b. የግል ጤና እንክብካቤ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ መድሀኒቱ የሚሰጥበት ቅድመ ሁኔታዎችን ማርቀቅ እና ለተገቢ ሰራተኞች፣ በተጨማሪም ለባስ ሹፌሮችን እና ለእረዳቶችን ዕቅዱን ማሳወቅ

   c. ከወላጅ/አሳዳጊ ተገቢ የሆነውን መድሀኒት እና የመስጫ መሳሪያ በማግኘት የሚከተለውን ማካተት፦

      i. ለሁለት ጊዜ የሚሰጥ ኤፒንፈሪን (epinephrine) ለተጨማሪ መድሀኒት መጠን ትዕዛዝ ሲኖር ወላጅ/አሳዳጊ ያቀርባል

      ii. በጤና ክፍል ሰራተኛ መድሀኒቱ ጥቅም ላይ እንደዋለ ወይም ቀኑ

እንዳለፈበት ማሳወቂያ ሲደርሰው/ሳት ወላጅ/አሳዳጊ ኤፒንፈሪን (epinephrine) መቀየር

iii. ወላጅ/አሳዳጊ ጥቅም ላይ ያልዋለ የተማሪን ኤፒንፈሪን (epinephrine) በትምህርት አመት መጨረሻ ላይ ከጤና ክፍል መውሰድ

d. የ MCPS ቅፅ Form 525-14 መጨረስ እና መሙላት፡- በምርመራ አናፊላክሲስ *(anaphylaxis)* የተገኘበት/ባት ተማሪን የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤን ማድረግ፣ በመድሀኒት አሰጣጥ መዝገብ ሰነድ ወይም ማስታወሻ ላይ

4. SCHN የጤና ክፍል ዝርዝርን MCDHHS 3190 በመጠቀም የመያዝ ሀላፊነት አለበት፣ የታወቀ አናፍላክሲስ *(anaphylaxis)* /ከባድ የአለርጂክ ምላሾች *(Reactions)* ያለባቸው ተማሪዎች መረጃ መለየት፣ የሚታወቅ አናፊላክሲስ (anaphylaxis) ለአለባቸው ተማሪዎች፣ የከባድ አለሪጂ/አናፊላክሲስ (anaphylaxis) ምላሽ (reaction) ማሳያዎችን እና ምልክቶችን ጨምሮ፣ እና አውቶማቲክ-መውጊያ ያላቸው ኤፒንፈሪን (epinephrine) አጠቃቀም ላይ የሰለጠኑ የት/ቤት ሰራተኞችን ስም። SCHN የዚህን ዝርዝር ግልባጭ ለዳይሬክተሩ/ሯ እና ተገቢ ለሆኑ የሰራተኛ አባላት የማሰራጨት ሀላፊነት አለበት። አንድ ግልባጭ ደግሞ በት/ቤቱ የድንገተኛ ጊዜ ቁሳቁሶች ማስቀመጫ ውስጥ መቀመጥ አለበት።

C. አውቶማቲክ-መውጊያ ያለው ኤፒንፈሪን (epinephrine) ማግኘት፣ ማስቀመጥ እና መቀየር

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ጤና እና የሰው አገልግሎቶች በ MCPS ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ኤፒንፈሪን (epinephrine) የሚያዝ ግለሰብ የመመደብ ሀላፊነት አለበት።

2. OSESS እና SHS በመተባበር የኤፒንፈሪን (epinephrine) ማግኘት፣ ማስቀመጥ እና መቀየርን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ቅደም-ተከተሎችን ያዘጋጃሉ።

D. የድንገተኛ ጊዜ መድሀኒት አሰጣጥ እና ክትትል

1. ኤፒንፈሪን (epinephrine) የሚሰጠው በት/ቤት የሚገኙ ከሆነ በ SHS ሰራተኛ ይሆናል። የ SHS ሰራተኛ በማይኖርበት ጊዜ፣ አውቶማቲክ-መውጊያ ያለው ኤፒንፈሪን (epinephrine) የሚሰጠው በተመረጡ ት/ቤት-መሰረት ያደረጉ ስልጠና የወሰዱ ሰራተኞች ይሆናል።

2. በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ፣ ኤፒንፈሪን (epinephrine) ሲሰጥ፣ ወደ 911 እና ወላጅ/አሳዳጊ ጋር መደወል አለበት።

3. አንድ ተማሪ በት/ቤት ኤፒንፈሪን (epinephrine) ከተሰጠው/ጣት በኋላ፣ SCHN እና፣ እንደ አስፈላጊነቱ፣ ዳይሬክተር/ተወካይ፣ በመተባበር ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ክትትል ያደርጋሉ፣ ይሄም ተደራሽነትን እና ትምህርት በመስጠት፣ እንደ አስፈላጊነቱ፣ ልዩ የጤና ፍላጎቶች ለአሏቸው ተማሪዎች የድንገተኛ ህክምና እንክብካቤ ቅደም-ተከተሎችን በሚመለከት ነው።

E. አውቶማቲክ-መውጊያ ያለው ኤፒንፈሪን (epinephrine) በግል-ለመውሰድ ፈቃድ የተሰጣቸው ተማሪዎች

ሀላፊነት የሚሰማቸው እና በእድገት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የራሳቸውን አውቶማቲክ-መውጊያ ያለው ኤፒንፈሪን (epinephrine) በግል-መውሰድ የሚችሉት በጤና እንክብካቤ ሰጪያቸው የሚመከር ከሆነ እና በ SCHN ከተፈቀደ ነው።

1. የMCPS ቅጽ 525-14: በምርመራ አናፊላክሲስ *(Anaphylaxis)* የተገኘበት/ባት ተማሪን የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤን ማድረግ፣ መሞላት እና መፈረም ያለበት በጤና እንክብካቤ ሰጪ ነው፣ ይሄም የሚያሳየው አውቶማቲክ-መውጊያ ያለው ኤፒንፈሪን (epinephrine) ተማሪው/ዋ መያዝ እና በግል-መውሰድ መቻሉን/ሏን ነው።

2. SCHN የተማሪውን/ዋን መድሀኒት በግል-መውሰድ ብቃት መመዘን እና መፍቀድ አለበት።

3. ተማሪው/ዋ አውቶማቲክ-መውጊያ ያለው ኤፒንፈሪን (epinephrine) በግል-ሲወስድ/ስትወስድ፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች፣ በተገቢ የሆኑ የት/ቤት ሰራተኞች እና በ SCHN ለጤና ክፍል ወይም ለት/ቤት ሰራተኞች ማሳወቅ እንደሚገባ መመሪያ ሊሰጠው/ጣት ይገባል፣ ይሄም 911፣ እንዲሁም ወላጅ/አሳዳጊ ጋር ለመደወል ያስችላል።

F. ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች

ሁሉም ኤፒንፈሪን (epinephrine) መጠቀሞች (MCPS/SCHN-የቀረቡ ወይም በተማሪ-የቀረቡ) በሚከተለው መንገድ ሪፖርት መደረግ አለባቸው፦

1. ዳይሬክተሩ/ሯ፣ ወይም ተወካዩ/ይዋ፣ አሳሳቢ ክስተትን ሪፖርት የማድረጊያ ቅደም-ተከተሎችን ይከተላሉ፣ ይሄም የተገለፀው በ MCPS ደንብ COB-RA፣ አሳሳቢ ክስተትን ሪፖርት ማድረግ ላይ ነው።

2. ዳይሬክተሩ/ሯ፣ ወይም ተወካዩ/ይዋ፣ ከ SCHN ጋር አብሮ በመስራት፣ በማንኛውም ኤፒንፈሪን (epinephrine) ለተማሪ ወይም ለሰራተኞች አባል በሚሰጥበት ወቅት፣ በሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ክፍል (MSDE) በሚጠበቀው መሰረት መረጃ ይሰበስባሉ፣ በሚከተለው መንገድ፦

   a. SCHN የሚያስፈልገውን መረጃ ሪፖርት ያደርጋል በ SHS አናፊላክሲስ *(Anaphylaxis)*/ኤፒንፈሪን *(epinephrine)* አሰጣጥ ሪፖርት ማድረጊ ስርዓት (AiRS) እና ለዳይሬክተሩ/ሯ መፈረሚያ ግልባጩን ያትማል።

   b. ዳይሬክተሩ/ሯ ወይም ተወካዩ/ይዋ የተፈረመበትን ሪፖርት ግልባጭ በሚከተለው መንገድ ያሰራጫል/ታሰራጫለች፦

      i. የተማሪ ጤና ሪኮርድ/ማህደር

ii. የተማሪ አገልግሎቶች ክፍል (DSS)

iii. የት/ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት

3. በ MSDE የተቀመጡትን የሪፖርት ማድረጊ መስፈርቶች ለማክበር DSS እና SHS በትብብር ይሰራሉ።

G. ለቤተሰብ ማሳወቅ

DSS ለተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በየአመቱ የማሳወቂያ መንገድን ያዘጋጃል እና ይተገብራል፣ ስለ የቦርድ ፖሊሲ JPD፣ ይሄም አናፊላክሲስ *(Anaphylaxis)* ለገጠማቸው ተማሪዎች የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ እና ስለ እዚህ ደንብ።

የደንቡ ታሪክ፦ በቀድሞ ደንብ ቁጥር 52514፣ የተሻሻለው ኦክቶበር 1982፤ የተከለሰው ኤፕሪል 1፣ 2008፤ የተሻሻለው ጁን 20፣ 2013።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org